VI ÄR EN DEL AV
REGION STOCKHOLM

# ማንኛዉም ጥያቄ አሎት?

እባኮትን AMEL፣ በግርዛት የተጠቁ ሴቶች ክሊኒክ ያግኙ።
ስልክ ቁጥር: + 46 (0)8 123 627 00

www.sodersjukhuset.se/amelmottagningen
amelmottagningen.sodersjukhuset@regionstockholm.se

**አድራሻ:** ሶድሪስጁኩስት። የማህፀን ህክምና መቀበያ:

**ሳብወይ:** ስካንስቱል። ወደ ሶድሪስጁኩስት የሚሀድ አዉቶቢስ 3።

**የስልክ ጥሪ ሰዓታት፡**
ሰኞ-ማክሰኞ kl.08-12፣ 13-15

ዓርብ kl.08-12።

በተጨማሪም በ1177 ቫርድጉዲን ኢ-አገልግሎት ሊያገኙን (የጤና እንክብካቤ ኢ-አገልግሎት)ይችላሉ።እባኮትን www.1177.se ይጠቀሙ

በተጨማሪም በ1177 ቫርድጉዲን በቀን 24 ሰዓት ምክር ማግኘት ይችላሉ ። ስልክ ቁጥር 1177



Fotogruppen januari 2023

SÖDERSJUKHUSET

SJUKHUSBACKEN 10, 118 81 STOCKHOLM, TEL 08-123 610 00
SL Buss 3, 4, 164, PENDELTÅG STOCKHOLM SÖDRA
WWW.SODERSJUKHUSET.SE

## ምን ዓይነት ድጋፍና ህክምና ማግኘት ይችላሉ?

የምናቀርባቸዉ ድጋፎች በእርሶ ይወሰናሉ እንዲሁም የሚያካትቱት:

ከደህንነት ባለሙያ ጋር መነጋገር

ስለ ልምዶ ማዉራት ከፈለጉ፣ ከደህንነት ባለሙያ ጋር መገናኘት የችላሉ፡፡

**ምርመራ**

ካሎት ሁኔታ አንፃር የተለያዩ የማህፀን ምርመራዎች እናቀርባለን፡፡

**ቀዶ ጥገና**

የማህጸኖ መግብያ በጣም ጠባብ ከሆነ፣ የመክፈት ቀዶ ጥገና በማድረግ ልናግዞት እንችላለን፡፡ ምን ያህል እንደሚከፈት ለመወሰን፣ በማህጸን ባለሙያ ድጋፍ የሚወሰን ይሆናል፡፡ በተጨማሪም፣ በወሊድ ግዜ ቀዶ ጥገና የሚያስፈልገዉ ጉዳት ሊፈጠር ይችላል፡፡ ቀዶ ጥገናዉ የሚካሄደዉ የመጀመርያ ጉብኝት በኋላእንጂ በመጀመርያዉ ቀን አይደለም፡፡ በቀዶ ጥገናዉ ግዜ እዲተኙ ወይ ማደንዘዣ ሊደረግሎት ይችላል፡፡ ቀዶ ጥገናዉ ሙሉ በሙሉ ህመም የለዉም፡፡ አብዛኛዉ ግዜ በሆስፒታል ግማሽ ቀን ሊያሳልፉ ይገባል፡፡

## የስዊድን ህግ

በስዊድን ከ1982 ጀምሮ የሴት ልጅ ግርዛት ተከልክሏል፡፡

1 § ፍቃድ ቢሰጥም ባይሰጥም በሴቶች ዉጫዊ ሀፍረተ ስጋ ላይ መግረዝ ወይ ሌሎች ዘላቂ ለዉጦች (ግርዛት) ለማምጣት ሂደቶችን ማካሄድ የለባቸዉም፡፡

ግርዛት የደረሰባቸዉ ሴቶች ራሳቸዉ ወይ ከእናቶች ማእከል፣ የወጣቶች ማእከል፣ የማህፀን ክሊኒክ ወይ ከቤተሰብ ዶክተር ሪፈራል ፎርም በማምጣት በክሊኒኩ መመዝገብ ይችላል፡፡

## በክሊኒኩ ማን እየሰራ ነዉ?

ሴት የማህፀንና ባለሙያዎችና የደህንነት ባለሙያዎች እዚህ ይሰራሉ፡፡ አስፈላጊ ከሆነ፣ ሴት አስተርጓሚ ባለሙያዎች እንጠቀማለን፡፡ ይህ አለመግባባትን ለማስቀረት ነዉ፡፡ ስለዚህ ለማስተርጎም ጓደኞች ወይ ዘመድ መጠቀም አይቻልም፡፡ ሁሉም ጉዳዮች በሚስጥር ይያዛሉ፡፡

## በመጀመርያዉ ጉብኝት ምን ይፈጠራል?

ስለ ሁኔታዎ ለመነጋገር የማህፀን ባለሙያዋን ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም ሊያገኙት ስለሚችሉት ድጋፍ መረጃ ልትሰጦት ትችላለች፡፡ አስፈላጊ ከሆነ የማህፀን ምርመራ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

## አብዛኛዉ ግዜ ሴቶች ለምን ድጋፍ ይፈልጋሉ?

ሴቶች ድጋፍ የሚፈልጉባቸዉ ተመሳሳይ ችግሮች:

- የማህፀን አከፋፈት በጣም ስለሚጠብ በፆታዊ ግንኙነት ግዜ መታመም፡፡
- ሽንት ለመሽናት መቸገር፡፡
- በወር አበባ መቸገር፡፡
- የማህፀን ጤና ከትትል፡፡
- በግርዛቱ ግዜ ምን እንደተደረገ ለማወቅ፡፡
- ስለ ግርዛት ማዉራት አስፈላጊነት፡፡
- ስለ ቀጣይ እርግዝናና ወሊድ ጥያቄ፣ ለምሳሌ የሚያስፈልጉትን ዝግጅቶች ምንነት፡፡
- ስለመከላከያ ማማከር
- ከግርዛት ጋር ያልተያያዙ ሌሎች የማህፀን መዛባቶች

# እንኳን ወደ Amel በግርዛት የተጠቁ ሴቶች ክሊኒክ በደህና መጡ




SÖDERSJUKHUSET